የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBI IC OF ETHIOPIA

አሥራሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12[th] Year No. 10
ADDIS ABABA 23[rd] December 2005

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፬፻፹/፲፱፻፺፰ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፫፻፳፭

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No. 480/2005**

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation…. Page 3325

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፹/፲፱፻፺፰

## በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት እ.ኤ.አ. ማርች ፪ ቀን ፪ሺ፭ በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የተደረገውን ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፹/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 480/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVEREMENT OF THE REPUBLIC OF TURKEY FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

**WHEREAS,** an Agreement for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income (the Agreement) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the republic of Turkey in Addis Ababa on the 2[nd] day of March 2005;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Agreement for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income on its meeting held on the 6[th] December 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows;

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No.480/2005."

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቱርክ ሪፐብሊክ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ማርች ፪ ቀን ፪ሺ፭ በአዲስ አበባ የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችለው ስምምነት ፀድቋል።

፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Turkey for the Avoidance of Double Taxation with Respect to Taxes on Income signed on the 2nd day of March 2005 is ratified.

**3. Power of the Minister of Finance and Economic Development**

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the Agreement in cooperation with the concerned Government organs.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 23rd day of December 2005**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት